የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

## ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ. 250725

ቀን ፡- ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- ወ/ሮ ውዴ ዘለቀ - ጠበቃ ደስታ ገብሩ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አታቱ ኢርኮ - ጠበቃ ባልካቸው አባትነህ ቀረቡ

2. የሟች አቶ ደረጀ ወ/ዮሐንስ ወራሾች

2.1. ሕፃን ሰብለ ደረጀ ሞግዚት አመልካች ጠበቃ

2.2. ዘሚካኤል ደረጀ አማረ አሞኘ -ቀረቡ

2.3. ሜላት ደረጀ

2.4. እዮብ ደረጀ ጠበቃ ባልካቸው አባትነህ ቀረቡ

2.5. አናንያ ደረጀ

2.6. አዛርያ ደረጀ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍርድ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አይገለግልም!

ጉዳዩ በኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመት ሳይሰጠው በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ምደባ የተደረገለት ሰው የሚሰጠው ውሳኔ ውጤትን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ እንደተረዳነው 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ባደረጉት ክርክር ጋብቻ ላይ የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ የጋራ ንብረት እንዲካፈሉ በተሰጠው ውሳኔ አመልካች መብቴን ይነካል በማለት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የመቃወሚያ ማመልከቻ ማቅረባቸውን ተከትሎ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 87587 ላይ ክርክር ተደርጎ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ በመዝገብ ቁጥር 248571 ግራቀኙን አከራክሮ የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች ማመልከቻ መሠረት የሰጠውን አዲስ ውሳኔ በመሻር አስቀድሞ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ በተጠሪዎች መካከል የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 233093 የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 12 ቀን 2015 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ላይ ከተሰየሙት ሦስት ዳኞች መካከል በ3ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየሙት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት በሕገ-መንግስቱና በአዋጅ ቁጥር 1233/2013 መሠረት ሹመት ያልተሰጣቸው በመሆኑ ውሳኔ ለመስጠት አይችሉም የሚልና የሥረ-ነገር ክርክሩን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔው የተሰጠው የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔው የሰጠው ባልተሟላ ችሎት ነው በሚል የቀረበውን አቤቱታ በመቀበል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት አዟል፤ በችሎቱ ከተሰየሙ አምስት ዳኞች መካከል ሁለቱ ባሰፈሩት የማስማሚያ ሃሳብ ጉዳዩ ባልተሟላ ችሎት የታየ ነው ወይስ አይደለም የሚለው የፌዴራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 26/2/ ሕገ-መንግስታዊ መሆን አለመሆንን የሚመለከት በመሆኑ ችሎቱ ይሕንን ነጥብ አድርጎ ሊያከራክርበት አይገባም ብለዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ እና ከ2.3 እስከ 2.6 ድረስ ያሉት ተጠሪዎች አንድ ላይ ነሀሴ 22 ቀን 2015 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ጉዳዩ አስቀድሞ በሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 140903 ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆነ ድጋሜ ሊታይ አይገባም፣ ጉዳዩም የክስ ምክንያት የለውም በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ሰበር ችሎቱ ባልተሟላ ችሎት ታይቷል በሚል በያዘው ነጥብ ላይ ያቀረቡት መከራከሪያ በፌዴራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 26/2/ መሠረት የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ዳኛን መመደብ ይችላል፣ በዚህ መሠረት በሰጠው ምደባ አግባብ የተከናወነ ስለሆነ ስህተት አልተፈጸመብትም፣ አመልካች ዳኛ ምደባው ተገቢ አይደለም ካሉ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታ አቅርበው ዳኛው እንዲነሱ ሳያደርጉ ውሳኔ ሲሰጥ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ሕጋዊነት የለውም፤ ውሳኔው ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ 2.1 እና 2.2. ላይ የተሰየሙት ተጠሪዎች በበኩላቸው ነሀሴ 22 ቀን 2015 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ባልተሾሙ ዳኛ የተሰጠው ውሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸጸምዓለማአ የገለግልም!

ሕገ-መንግስቱን መሠረት ያላደረገ ስለሆነ ሊሻር ይገባዋል ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም በኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመት ሳይሰጠው በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ምደባ የተደረገለት ሰው የሚሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከተሰየሙት ዳኞች መካከል በሦስተኛ ተራ ቁጥር የተሰየሙት ዳኛ በፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ምደባ የተደረገላቸው እንጂ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት በኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመት ያልተሰጣቸው በመሆኑ የሚሰጡት ዳኝነት ሕጋዊ ውጤት የለውም በሚል ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከተሰየሙት ዳኞች መካከል በሦስተኛ ተራ ቁጥር የተሰየሙት ዳኛ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾሙ ሲሆን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት ግን ሹመት አላገኙም፡፡ በጉዳዩ ላይ የተሰየሙት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በፌዴራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 26/2/ መሠረት በተሰጣቸው ጊዜያዊ ምደባ መሠረት ነው፡፡ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሚሰጠው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ መብቱ የተነካ ወገን ጉዳዩ በዳኝነት ክለሳ መንገድ እንዲታይለት ለፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ ነገር ግን የዳኝነት ክለሳ የሚቀርበው ቀጥታ ለሰበር ችሎት ሳይሆን ከሰበር ችሎቱ በታች ላለ መደበኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 214219 /ያልታተመ/ ላይ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የዳኝነት ክለሳ እንዲታይ የቀረበ አይደለም፡፡ ለዚህ ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታ በጉባዔው በጊዜያዊነት ምደባ የተሰጠው ሰው በፍርድ ተሰይሞ የሚሰጠው የዳኝነት ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት ያለው መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በሕግ ሹመት አግኝቶ ሕጋዊ ውጤት ያለው ውሳኔ ሊሰጥ በሚችል ዳኛ/ችሎት የተሰጠ ውሳኔ መሆን አለመሆኑን የመመርመር ኃላፊነት የፍርድ ቤቱ በመሆኑ ጉዳዩን እንደሚከለው ተመልክተነዋል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 50(2) ላይ የመንግሥት አካላትን የሥልጣን ክፍፍል መርህ (principle of separation of powers) የተመለከተ ሲሆን በሦስቱ የመንግሥት አካላት በሆኑት ሕግ አውጭው፣ ሕግ አስፈጻሚው እና የሕግ ተርጓሚው መካከል የሥልጣን ክፍፍል ያለ ቢሆንም በመካከላቸው የእርስ በእርስ ቁጥጥር (check and balance) ከሌለ ተቋማቱ በሕግ የተጣለባቸውን የዜጎችን ሠብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ማክበርና ማስከበር አይችሉም፡፡ የእርስ በእርስ ቁጥጥሩ ጣልቃ መግባትን ካስከተለ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝንና የተጣለባቸውን ግዴታ እንዳይወጡ ሊያደርጋቸው ስለሚችል ቁጥጥሩ በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት አግባብ መፈጸም አለበት፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 81(2) መሠረት የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች /በደንጋጌው የእንግሊዘኛ ቅጂ በግልጽ 'other Federal judges' የሚለውን ይመለከቷል/ ሹመትን በተመለከተ በዳኞች አስተዳደር

ጉባዔ የቀረቡለትን እጩዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል በሚል ይደነግጋል፡፡ ይሕም የዳኝነት ሹመት የሚሰጠው ሕግ አውጪው ብቻ ስለመሆኑና አንዱ ፍርድ ቤት ላይ የተዘረጋወ የቁጥጥር ሥርዓት መገለጫ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፌዴራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 2/7/ ላይ የፌዴራል ዳኞች ማለት በኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾሙ ዳኞች ማለት ነው በሚል መገለጹም በሕገ-መንግስቱ የተቀመጠውን ሥርዓት ተከትሎ ሹመት የሚገኘው ከምክር ቤቱ ብቻ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 8/1/ እና /2/ ላይ ለፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተሰጠው ሥልጣን ዕጩ ዳኞችን በመመልመል ለሹመት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በማቅረብ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ያደርጋል የሚል ሲሆን በአዋጁ ከአንቀጽ 20-23 የተመለከተውም ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በየፍርድ ቤቱ እርከን ዳኛ ሆኖ ለመስራት በሕጉ የተመለከቱ መስፈርቶችን ከማሟላት ባለፈ በየደረጃው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመት ማግኘት የግድ የሚል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ አዋጅ ቁጥር 1233/2013 በቋሚነት ዳኛ ሆኖ ለመስራት ሹመት የሚሰጠው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ስለመሆኑ መደንገጉ ሕገ-መንግስቱን የዘረጋውን የእርስ በእርስ ቁጥጥር ሥርዓት በማክበር የወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 24 ላይ ጊዜያዊ ዳኛ ሆኖ ለመሾም እንኳን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ሹመት የሚያስፈልግ መሆኑ መመልከቱ ዳኛ ሆኖ ሕጋዊ ውጤት ያለው የዳኝነት ሥራ ለመስራት ሹመት ለመስጠት ሥልጣን ካለው አካል መሾምን የሚጠይቅ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በፌዴራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 26 ላይ የዳኞች የደረጃ እድገትና ዝውውር በሚል በተቀረጸው ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አስፈላጊ ሆኖ ሲሆንና በቂ ምክንያት ሲኖር ዳኛ በፍቃደኝነት ከአንድ የፌዴራል ፍርድ ቤት ደረጃ ወደ ሌላ የፍርድ ቤት ደረጃ በጊዜያዊነት <u>መድቦ</u> /ሠረዝ የተጨመረበት/ ሊያሰራ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ይሕ ድንጋጌ እንደማንኛውም ሕግ ሕገ-መንግስታዊ ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 2/7/፣ አንቀጽ 8/1/ እና /2/፣ አንቀጽ 20-23 እና አንቀጽ 24 ዳኛ ለመሆን በየፍርድ ቤቱ እርከን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመት ማግኘት የግድ ስለመሆኑ የተደነገገ በመሆኑ የአንቀጽ 26/2/ ውጤትም ከአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ሁሉም ድንጋጌዎች አዎንታዊ ውጤት በሚያገኙበት መልኩ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ አዋጅ ቁጥር 1233/2013 የዳኛ ሹመት እና የዳኛ ጊዜያዊ ምደባ የሚሰጠበትን ሁኔታ በተለያየ መንገድ ማስቀመጡ ሲታይ ዳኛ መሆን የሚቻለው በሹመት ብቻ ስለመሆኑ፣ ሹመቱ የሚሰጠውም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሆኑን ያስቀመጠ ሲሆን የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ደግሞ የዳኛ ዝውውርን በመመርመር ጊዜያዊ ምደባ ሊሰጥ እንደሚችል መመልከቱ ምደባ ሹመት የሚያስገኘውን ውጤት እንደማያሰጥ ሆኖ መቀረጹን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 2/16/ የተመለከተው የዳኝነት ሥራ መስራት የሚችለው ከላይ በሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመት የተሰጠው ዳኛ ነው፡፡

የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ዕጩ ዳኞችን መልምሎ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በኩል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለሹመት እንዲቀርቡ ማድረጉም ሆነ በአዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 24 እንደተመለከተው ጊዜያዊ ዳኛ ጭምር የሚሾመው በሕዘብ ተወካዮች ምክር ቤት መሆኑ መደንገጉ በሕገ-መንግስቱ ሆነ በአዋጅ ቁጥር 1233/2013 መሠረት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ለዳኛ ሹመት የመስጠት ሥልጣን የሌለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፤ ይሕም ጉባዔው በአዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 26/2/ የሚሰጠው ምደባ ከሹመት የተለየ ውጤት ያለው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ጉባዔው የሚሰጠው ምደባ በዳኛው ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆኑ መመልከቱ በአንድ በኩል ዳኛው ከተሾመበት የፍርድ ቤት እርከን ወደታች ወደሚገኝ ፍርድ ቤት በጊዜያዊነት ተመድቦ ስራ የሚያቃልልበት መንገድ መኖሩን የሚጠቁም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 26/1/ እንደተመለከተው በጊዜያዊነት የተመደበው ሰው ሊያከናውን የተፈለገውን ሥራ ጉባዔው በመመሪያ በማመልከት ሥራውን ማስፈጸም የሚችል መሆኑን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ምደባው ዳኛው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባልተሸመበት ከፍ ወዳለው የፍርድ ቤት እርከን ሹመት የማስገኘት ውጤት የለውም፡፡

ዜጎች በነጻ ዳኝነት ተቋም መብታቸውን ማስከበር የሚችሉ ሲሆን ዳኞች በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት ያገኙትን የዳኝነት ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የመጨረሻ እና የሚከበር መሆኑ አንዱ መገለጫውም ውሳኔ የሚሰጠው በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት መሆኑ ነው፡፡ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 81/2/ መሠረት ዳኞች የዳኝነት ሥልጣን የሚያገኙት በምክር ቤቱ ቀርበው በየፍርድ ቤቱ እርከን ደረጃ ሹመት ሲያገኙ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በሕገ-መንግስቱ በሦስቱ የመንግስት አካሎች መካከል የተዘረጋውን የእርስ በእርስ ቁጥጥር የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 9 ላይ ስለሕገ-መንግስቱ የበላይነት ከተደነገገው የምንገነዘበው ነው፡፡ በሕገ-መንግስቱ በግልጽ የተሰጠ ሥልጣንና ኃላፊነት በውክልና ለሌላ አካል የሚተላለፍ የሚችል ካለመሆኑም በላይ በፌዴራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 2/7/፣ 8/1/ እና /2/፣ አንቀጽ ከ20-24 መሠረት ሹመት የሚሰጠው በምክር ቤት ብቻ ስለመሆኑ በሕጉ የተመለከተው ማክበርና ሕጋዊ ውጤት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ፍርድ ቤት የዜጎችን መበት ለማስከበር የተቋቋመ አካል ሲሆን የሕግ የበላይነትን ማስከበር የሚችለው በሕግ ብቻ ሲሰራ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች ውሳኔያቸውን በሕግ ሹመት በተሰጠው ዳኛ /በሕግ በተቋቋመ ችሎት/ ተገቢውን የሕግ ሥርዓት ተከትለው ካልሰሩ ውሳኔያቸው የአስገዳጅነት ኃይል የማይኖረው ከመሆኑም በተጨማሪ ዜጎች ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት (public trust) እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም በፍርድ በዳኝነት ተሰየሞ አስገዳጅነት ያለው ውሳኔ መስጠት የሚችለው በየፍርድ ቤቱ የእርከን ደረጃ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የተሾመ ዳኛ ብቻ መሆን ያለበት በመሆኑ ከዚህ ውጭ በምክር ቤት ሹመት ሳይሰጠው በዳኝነት ተሰይሞ መወሰን ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 25/2/ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከሦስት ባላነሱ ዳኞች ያስችላሉ፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው ዳኛ መሆን የሚቻለው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ በሚሰጥ ሹመት በመሆኑ አሁን በተያዘው ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ

ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሰይመው ውሳኔ ከሰጡ ዳኞች መካከል በሦስተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየሙት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት ሹመት ያልተሰጣቸው በመሆኑ ችሎቱ በሕግ ከተወሰነለት ቁጥር በታቻ በሁለት ዳኞች ውሳኔ መስጠቱን ያሳያል፡፡ ይሕም በሕግ የተመለከተው የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ ውሳኔ እንደተሰጠ ያረጋግጣል፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ያለበት ፍርድ በይግባኝ ካልተለወጠ የጸና እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡ በህግ የተቋቋመ የዳኝነት አካል ከነግድፈቱም ቢሆን የሰጠው ውሳኔ መከበር እና መፈጸም አለበት፡፡ ይህም አንዱ የህግ የበላይነት መገለጫ ነው፡፡ ነገር ግን በህግ የተቋቋመው የዳኝነት ተቋም በተለየም ከአንድ ዳኛ በላይ ሆኖ በሚሰየምበት ችሎት ከተፈቀደለት የዳኛ ቁጥር በታች ሆኖ ከተሰየመ ህጋዊ እና አስገዳጅ ውሳኔ ለመሥጠት ያለውን የአስገዳጅነት ሀይሉንና የህግ ከለላውን ያሳጣዋል፡፡ በአንድ በተሰየመ ችሎት የተለያየ እና የህግ ዕውቅናና መሰረት የሌለው ውሳኔ እንዲሰጥ ዕድል የሚከፍትና ዜጎች በዳኝነት አካሉ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በዚህ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 73696 ቅጽ 13 ላይ የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ የሚሠጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ህጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚገባ አይደለም በማለት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም የሥነ-ስርዓት ግደፈት ያለበት ውሳኔ የጸና የሚሆነው በተሟላ ችሎት ከተሠጠ ብቻ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባልተሟላ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሕጉንና የሰበር ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ ያልተከተለና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፤በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ እና ከ2.3 እስከ 2.6 ያሉት ተጠሪዎች ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው፣ ጉዳዩም የክስ ምክንያት የለውም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ በተመለከተ በይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በተሟላ ችሎት ውሳኔ ሲሰጥ የሚታይ ከመሆኑ ባለፈ ጉዳዩ በይግባኝ ደረጃ በተሟላ ችሎት ሳይታይ ሰበር ችሎቱ ውሳኔ የሚሰጥበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 233093 ሰኔ 10 ቀን 2015 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ በተሟላ ዳኛ /በተሟላ ችሎት/ በመመልከት በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት መሠረት አድርጎ እንዲወስን ጉዳዩን መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ የማያገለግል ነው!

- ውሳኔው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይተላለፍ፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- ውሳኔው ሐምሌ 02 ቀን 2016 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

# <u>የልዩነት ሀሳብ</u>

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 1 እና 3 የተጠቀሰው የችሎቱ ዳኞች አብላጫው ድምፅ በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ የልዩነት ሀሳባችንን እንደሚከተለው አሰፍረናል ፡፡

በመሰረቱ የዳኝነት ነፃነት መርህ ፍርድ ቤቶች የተጣለባቸውን ህገ መንግስታዊ ተልዕኮ እንዲወጡ የሚያስችላቸው በጥብቅ ሊከተሉትና ሊተገብሩት የሚገባ መሰረታዊ መርህ ነው፡፡በዘመናዊው የዳኝነት ፅንሰ ሀሳብ መሰረት የዳኝነት ነጻነት ባለቤት ዳኞች ብቻ ሳይሆኑ ፍርድ ቤቶችን እንደ ተቋም የሚያጠቃልል ሲሆን የዳኝነት ነፃነትን ከዳኞች አንፃር ብቻ ስናየው ዳኞች ካለምንም የውጪ ጣልቃ ገብነት፣ተፅዕኖና ግፊት የቀረበላቸውን ጉዳይ ህግንና ማስረጃን ብቻ መሰረት በማድረግ ለመወሰን ያላቸውን ነፃነት የሚወክል መሆኑን ከአጠቃላዩ የዳኝነት መርህ የምንረዳው ነው፡፡በዚህ ረገድ የዳኝነት ነፃነትን ለማረጋገጥ የዳኞች ምልመላና ሹመት፣እድገት፣ዝውውር፣የስራ ዘመን፣ዲሲፒሊን ፣ከስራ የማሰናበት ስርዓት እና የመሳሰሉት ተገቢው የህግ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ በዚህ አግባብም የዳኝነት ነፃነት የተረጋገጠበት የህግ ስርዓትን መገንባት ግቡ ያደረገ የህግ ስርዓት አንድ እጩ ዳኛ እንዴት እንደሚመለመልና ለሹመት ሊያበቁ የሚችሉ መስፈርቶች ምን እንደሆኑ፣ሿሚው አካል ማን እንደሆነ፣የሹመቱ ዘመን ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ፣ዳኛው ከተሾመ በኋላ እድገትና ዝውውሩ በምን መስፈርት እንደሚከናወን ፣የዲሲፒሊን እርምጃ እንዴትና በማን እንደሚወሰድ ፣ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉ ምክንያቶችና ሌሎች ነጥቦችን የሚደነግግ ግልፅና የተብራራ ህግ ሊኖረው የሚገባ መሆኑን ከአጠቃላዩ የዳኝነት ነፃነት መርህ የምንረዳው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮአረጋጋምዓለማእየገለግልም!

ሀገራት የሚከተሉት የዳኞች ምልመላና ሹመት ሂደት የዳኝነት ነፃነትን ለማረጋገጥ ያላቸውን ጥንካሬና ቁርጠኝነት የሚያሳይ መሰረታዊ መስፈርት ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን ከላይ ከተመለከተው ዝርዝር ሀሳብ የምንረዳው ነው፡፡በጀርመን፤ፈረንሳይና ሲውዲን የዳኞች ሹመት ለአስፈፃሚ አካል (Minstry of Justice) መስጠቱ እንዲሁም በአሜሪካ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞች በፕሬዝዳንቱ አቅራቢነት በሴኔት እንዲሾሙ መደረጉ በካናዳም ዳኞች የሚሾሙት በካቢኔው መሆኑ ሀገራቱ ከዳኞች ምልመላና ሹመት አንፃር የተለያየ ሂደት የሚከተሉ መሆኑን ይህንን ተከትሎም የዳኝነት ነፃነትን በማረጋገጡ ሂደት የተለያየ አካሄድን የተከተሉ መሆኑን ያሳያል፡፡ወደ ሀገራችን ስንመለስም የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ እንደሆነና ነጻ የሆነ የዳኝነት አካል በህገ መንግስት ዋስትና ተሰጥቶት የተቋቋመ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህግ መንግስት አንቀጽ 78/1/ እና 79/1/ ድንጋጌዎች መመልከቱ፤እንዲሁም ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸዉን ከማናቸዉም ተጽዕኖ ነጻ ሆነዉ በሙሉ ነፃነትና በህግ ብቻ ተመርተዉ መስራት እንዳለባቸዉም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 79/2 እና 3/ በግልጽ መመልከቱ፤ስልጣኑ delegate ሊደረግ የማይችል መሆኑን በሚያመለክት አግባብ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞችን ሹመት የማፅደቅ Inherent ስልጣን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 55(13) መሰረት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መስጠቱ ህገ መንግስታችን ከዳኞች ሹመት፤ምልመላና እድገት አንፃር ጥብቅ የሆነውን መንገድ የተከተለ መሆኑን ያሳያል፡፡በተለይም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሁንታን ያገኘ የዳኞች ሹመት በተለያየ የፍርድ ቤት እርከን ለመስራት መሰረታዊ መስፈርት መሆኑ በህገ መንግስቱ መመልከቱ ለሁሉም የፍርድ ቤት እርከን ዳኛ የሚመደበው በሹመት ነው የሚለውን መርህ ከሚከተሉት ህንድ፤ብራዚል፤ደቡብ አፍሪካ አሜሪካ እንግሊዝና ካናዳ ጋር ተመሳሳይ አይነት የህግ ስርዓት የገነባን መሆኑን ያሳያል፡፡

በህገ መንግስቱ አግባብ የተቃኘው የፌደራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 በአንቀፅ 20 እና ተከታዮቹ በየደረጃው ላሉት ፍርድ ቤቶች ተገቢውን የምልመላ መስፈርት የሚያሟሉ እጩዎች በዳኝነት የሚሾሙ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን በፌደራል ከፍተኛ እና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚሾመው ጊዜያዊ ዳኛም እንኳ ተገቢውን የምልመላ መስፈርት ማሟላቱ በ2/3ኛ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ድምፅ ሲረጋገጥ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊሾም የሚችል መሆኑ በአንቀፅ 24 መመልከቱ አዋጅ ቁጥር 1233/2013 በተለያየ የፍርድ ቤት እርከን ለመስራት በህጉ አግባብ የተፈፀመ የዳኞች ሹመት መሰረታዊ መስፈርት መሆኑን በማሳየት  ጥብቅ መስፈርትን የተከተለ መሆኑን የሚያሰይ ቢሆንም ህጉ በአንቀፅ 26(2) ጉባዔው አስፈላጊ ሲሆንና በቂ ምክንያት ሲኖር ዳኛ በፍቃደኝነት ከአንድ የፌደራል ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ደረጃ በጊዜያዊነት ሊያሰራ የሚችል መሆኑን ማመልከቱ በዚህ ረገድ አዋጁ ከዳኛ ሹመት ጋር በተያያዘ የተለየ ሂደትን የተከተለ መሆኑን ከድንጋጌው አጠቃላይ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡

በመሰረቱ ከሕገ-መንግሥታዊ ክርክሮች (constitutional disputes) ውጭ ማንኛውም በፍርድ ቤት ታይተው ሊወሰኑ የሚችሉ ጉዳዮች (justiciable matters) ላይ ፍርድ ቤቶች ዳኝነታዊ ክለሳ የማድረግ (judicial review) ተፈጥሮአዊ የሆነ ዳኝነታዊ ሥልጣን (inherent judicial power) አላቸው፡፡ከአዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንፃር ስናየው የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የእለት ተእለት ተግባሩን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸጸምዓለማአ የገለግልም!

ሲያከናዉን ተገቢውን ጥናት በማድረግና በማስደረግ አስተዳደራዊ ዉሳኔ  መስጠት የመጀመሪያው ሀላፊነቱ ሲሆን አንድ ዳኛ በዲሲፕሊን ምክንያት ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ከሥራ እንዲሰናበት ዉሳኔ መስጠት  ወይም በሕመም ምክንያት ዳኛዉ ተግባሩን በተገቢዉ ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ የመወሰን ስልጣኑ ክርክርና ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ እንዲሁም ማስረጃዎችን መዝኖ የአከራካሪዉን ጭብጥ መኖር አለመኖር ካረጋገጠ በኋላ የሚደርስበት መደምደሚያ በመሆኑ ይህ የዳኝነት-ነክ ሥልጣኑን ተጠቅሞ የደረሰበት መደምደሚያ በመሆኑ ይህ ውሳኔ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርምሮ ተገቢዉ ዉሳኔ ሊሰጥበት ከሚችል በስተቀር በልዩ ሁኔታ በሕግ እስካልተደነገገ ድረስ በመደበኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት የሚታይ ባለመሆኑ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በነዚህ ውሳኔዎች ላይ የዳኝነት ስልጣን ባይኖራቸውም መደበኛ ፍርድ ቤቶች በጉባኤው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ግን ስልጣን ያላቸው በመሆኑ (በሰ/መ/ቁ.214219፤ እና በተመሳሳይ መዝገቦች ላይ የተሰጡትን አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች ይመለከቷል፡፡) ጉባዔው ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማዛወር ካሰራቸው ዳኞች አንፃር በሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ አግባብነት ላይ ጥያቄ ከተነሳ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት ስልጣኑ የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ነው ብለን እናምናለን፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለውን ውዝፍ መዝገቦች ለማቃለል እንዲቻል አሁን ክርክር የተነሳባቸውን ዳኛ ጨምሮ አራት ዳኞችን የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የአዋጁን አንቀፅ 26(2) መሰረት በማድረግ  ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማዛወር ከአንድ አመት ላለነሰ ጊዜ አዛውሮ ማሰራቱ እና ክርክር የተነሳበት መዝገብም በዚሁ አግባብ እልባት ማግኘቱ ግልፅ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አሁን ክርክር የተነሳባቸውን ዳኛ ጨምሮ አራት ዳኞችን ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አዛውሮ ያሰራው በአንቀፅ 26(2) ጉባዔው አስፈላጊ ሲሆንና በቂ ምክንያት ሲኖር ዳኛ በፍቃደኝነት ከአንድ የፌደራል ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ደረጃ በጊዜያዊነት አዛውሮ ሊያሰራ የሚችል መሆኑን በማመልከት የተሰጠውን ስልጣኑን መሰረት በማድረግ ነው፡፡የአዋጁ አንቀፅ 26 በጥቅሉ የዳኞችን እድገትና ዝውውር የሚመለከት መሆኑ በድንጋጌው መግቢያ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በአንቀፅ 26(2) የዳኛውን ፈቃድ በማግኘት ከአንድ እርከን ወደ ሌላ ፍርድ ቤት በመዛወር የሚከወነው የዳኝነት ስራ ነው ተብሎ የሚወሰድ ሲሆን የዳኝነት ስራ ደግሞ በአዋጁ የትርጉም ክፍል በአንቀፅ 2(16) የጉዳዩን ፍሬ ነገር በመለየትና አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማዛመድ፣ ጭብጥ በመለየት፣ጉዳዮችን በማከራከር፣ አቤቱታ እና ምስክር በመስማት፣ ትዕዛዝ ፣ ብይን፣ ውሳኔ መስጠትና ማስማትን የሚያጠቃልል መሆኑ የተመለከተ በመሆኑ ጉባዔው አራት ዳኞችን ከከፍተኛ ፍርድ ቤት በማዛወር በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኛ የሚከናወንን መሰረታዊ የዳኝነት ስራን  ማሰራቱ በአዋጁ አንቀፅ 26(2) እና 2(16) የጋራ ንባብ መሰረት አግባብ ነው የሚለውን አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥቷል ከሚያስብል በስተቀር በሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊከለስና ዋጋ ሊያጣ የሚችል ውሳኔ ሰጥቷል የሚያስብል አይሆንም፡፡

ከዚህ ይልቅ በአዋጁ አንቀጽ 26(2) የተመለከተው ለጉባዔው ዳኛን ሳይሾም ከአንድ እርከን ወደ ሌላ ፍርድ ቤት በቂ ምክንያት ሲኖር አዛውሮ የማሰራት ስልጣን ፤ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 81(2) (በዳኝነት ለመስራት

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሾምን ጥብቅ ከሚደነግገው ድንጋጌ ) እና ከአንቀፅ 55(13) (የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞችን ሹመት የማፅደቅ Inherent ስልጣን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤ይህ ስልጣን delegate የሚደረግ አይደለም በማለት ከሚደነግገው ድንጋጌ) ጋር የሚቃረን ነው? ወይስ አይደለም? ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? በሚሉት ሕገ-መንግሥታዊ ክርክሮችን (constitutional disputes) በሚጋብዙ ጭብጦች ላይ የመወሰን ስልጣኑ የዚህ ችሎት ሳይሆን በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 62(2) እና በአዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀፅ 4(1)፤5፤6(2) መሰረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት በመሆኑ የአዋጁ ህገ-መንግስታዊ መሆን አለመሆን ለምክር ቤቱ ቀርቦ ተገቢው እልባት እንዲሰጠው ሊመራ ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረባዎቻችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ የማይውል ነው!